# የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን መካነ ኢየሱስ

# መሠረተ እምነት

# መካነ ኢየሱስ ማለት ምን ማለት ነው?

- **መካነ ኢየሱስ** ማለት የኢየሱስ መኖሪያ ሥፍራ ማለት ሲሆን የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን ቋሚ ስም ነው፡፡
- **ወንጌላዊት** ማለት ንጹህ የሆነውን የወንጌል ትምህርት የምታስተምርና የምትጠብቅ፣ በእግዚአብሔር ቃል መሠረት ቅዱሳት ምስጢራትን በሚገባ የምትፈጽም ቤተክርስቲያንን የሚያመለክት ነው፡፡

- የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን መካነ ኢየሱስ **‹‹የሰውን ሁለንተና ማገልገል /Serving the Whole Person/**›› በሚል መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርሆ የተቋቋመች ናት፡፡
- የሰውን ሁለንተና ማገልገል ማለት የሰውን ልጅ መንፈሳዊና አካላዊ ሕይወት መንከባከብና ማሳደግ ማለት ነው፡፡



ኢየሱስ በምድረ በዳ ካስተማራቸው በኋላ በሁለት ዓሣና በአምስት እንጀራ 5 ሺህ ሰዎችን የመገባቸው ክፍል የሰውን ሁለንተና ማገልገል የሚለውን ሐሳብ ይደግፋል፡፡ ማር. 6፡38



# መዋቅር

የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን መካነ ኢየሱስ

ማዕከላዊ ደቡብ ሲኖዶስ

ሆ.ዞ ሰበካ

-- ማህበረ ምዕመናን

# መካነ ኢየሱስ እንደ እግዚአብሔር ቃል ምን ታምናለች ምንስ ታስተምራለች?

# 1. ትምህርተ ሥላሴ

- አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ እናምናለን፡፡



- የሥላሴ አስተምህሮ የክርስትና እምነት መሠረት ነው፡፡
- ስለ እግዚአብሔር ማንነት ለማወቅ፣ እርሱ ከእኛ ጋር በምን መልኩ ህብረት እንደሚያደርግና እኛም ከእርሱ ጋር እንዴት ህብረት ማድረግ እንዳለብን ለመረዳት እጅግ አስፈላጊ አስተምህሮ ነው፡፡
- እግዚአብሔር እንዴት በአንድ ጊዜ አንድና ሦስት ይሆናል? የሚሉ ጥያቄዎችን ሰው በዚህ ውስን አዕምሮ ሙሉ በሙሉ ለማስረዳት ቢከብድም የተጻፈውን ያህል እንማራለን፡፡
- ዘፍ. 1፡26 ‹‹**እግዚአብሔርም አለ፦ ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር፤** … ››
- ኢሳ. 6፡8 ‹‹**የጌታንም ድምፅ፡- ማንን እልካለሁ? ማንስ ይሄድልናል? ሲል ሰማሁ፡፡**›› ‹‹**ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ**›› 6፡3

- የሥላሴ አስተምህሮ ማለት እግዚአብሔር ሦስት የተለያዩ አካላት ማለትም አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ የሆነ አንድ አምላክ ነው ማለት ነው።
- ዮሐ. 3፡16 ላኪው አብ፣ የተላከው ወልድ መሆኑን ይናራል።
- ዮሐ. 16፡7-10 ወልድ መንፈስ ቅዱስን ሲልክ፣ መንፈስ ቅዱስ በእርሱ ስለማያምኑና፣ ወደ አብ ስለሚሄድ ይፈርድባቸዋል።
- በሌላ አገላለፅ እግዚአብሔር በማንነት፣ በመለኮትና በህልውና አንድ ሲሆን በአካል ግን ሦስት ነው ማለት ነው።
- ይህ አተረጓጎም ሦስት ጠቃሚ እውነቶችን ያዘለ ነው፦

1. አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ሦስት የተለያዩ አካላት ናቸው፤ ዮሐ. 16፡13-15
2. እያንዳንዱ የሥላሴ አካል ሙሉ አምላክ ነው፤
3. እግዚአብሔር አንድ አምላክ ነው።

# ስለ ሥላሴ የአትናቴዎስ የሃይማኖት መግለጫ (13-18)

- አብ ሁሉን የሚችል ነው፣ ወልድ ሁሉን የሚችል ነው፣ መንፈስ ቅዱስ ሁሉን የሚችል ነው፡፡
- አብ አምላክ ነው፣ ወልድ አምላክ ነው፣ መንፈስ ቅዱስ አምላክ ነው፡፡ (ፊል. 1፡2፤ ቲቶ. 2፡13፤ የሐዋ. 5፡3-4)
- ሆኖም አንድ አምላክ እንጂ ሦስት አማልክት አይደሉም፡፡
- አብ ጌታ ነው፣ ወልድ ጌታ ነው፣ መንፈስ ቅዱስ ጌታ ነው፡፡ ሆኖም አንድ ጌታ እንጂ ሦስት ጌታ አይደሉም፡፡
- ማቴ. 28፡19-20 ‹‹ስም›› አንዴ ስለተጠቀሰ አንድ አምላክ መኖሩን አመልካች ነው፡፡

# ስለ ሥላሴ የአትናቴዎስ የሃይማኖት መግለጫ (25-28)

- ‹‹ሦስቱ አካላት በእኩልነትና በዘላለማዊነት አንድ ናቸው፡፡ … ሦስቱ አካላት በአንድ መለኮት አንድ አምላክም በሦስት አካላት ይመለካል፡፡
- ለመዳን የሚፈልግ ሁሉ ስለ ሥላሴ እንደዚህ ማሰብ ይገባዋል፡፡
- ከዚህም ሌላ የዘላለምን ዳህንነት ለማግኘት የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን በሥጋ መገለጥ በእውነት ማመን አስፈላጊ ነው፡፡
- ምክንያቱም ትክክለኛው እምነት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ አምላክም ሰውም መሆኑን አምነን ማስታወቅ ነው፡፡››
- እርሱም ከዘመናት አስቀድሞ ከአብ የተወለደ አምላክ ከእናቱም በሥጋ በዓለም የተወለደ ሰው ነው፡፡
- የሚያስብ ነፍስ ያለችውና የሰውን ሥጋ የለበሰ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው ነው፡፡››

# 2. መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ነው

- የብሉይ ኪዳን 39 + የአዲስ ኪዳን 27 = 66ቱ ቅዱሳት መጽሐፍት ፡-

1. መጽሐፍ ቅዱስ ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው የጻፉት የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን እናምናለን፡፡ 2 ጴጥ. 1፡21 ‹‹**ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና፥ ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ።**››
2. ለእምነትና ለሕይወት የሚጠቅም የእግዚአብሔር ቃል ነው፡፡ 2 ጢሞ. 3፡16-17 ‹‹**የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል።**››
3. ምንም ስህተት የሌለበት የሕይወት መመሪያን መሪ እንደሆኑ አምና በመቀበል በእምነቷ  ታረጋግጣለች፡፡

# 3. ቅዱሳት ምስጢራት የጸጋ መቀበያ መሣሪያዎች መሆናቸውን እናምናለን

- **ቅዱሳት ምስጢራት** ማለት በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተመሠረቱና ለደህንነት አስፈላጊ የሆኑ መንፈሳዊ ክንዋኔዎች ናቸው፡፡
- ቅዱሳት ምስጢራት በሚታዩ ነገሮች የማይታየውን ጸጋ መቀበያ መሣሪያዎች ናቸው፡፡ እነዚህም፡-

1. ቅዱስ ጥምቀት
2. ቅዱስ የጌታ ራት ናቸው፡፡





# 3.1. ቅዱስ ጥምቀት

- ጥምቀት ተራ ውሃ አይደለም፡፡
- በእግዚአብሔር ትዕዛዝ ውስጥ የታቀፈና ከእግዚአብሔር ቃል ጋር የተጣመረ ውሃ ነው፡፡
- ይህ የእግዚአብሔር ቃል ማቴ. 28፡19 **‹‹እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።››**
- በጥምቀት እግዚአብሔር ጸጋውን ለሰው ያቀርባል፡፡ ሕጻናትም ሆኑ አዋቂዎች ወደ ጥምቀት በሚቀርቡበት ጊዜ የጸጋ ተካፋዮች ይሆናሉ፡፡
- የሐዋ. 2፡39 **‹‹የተስፋው ቃል ለእናንተና ለልጆቻችሁ ጌታ አምላካችንም ወደ እርሱ ለሚጠራቸው በሩቅ ላሉ ሁሉ ነውና አላቸው።››**

# የጥምቀት መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረቶች

- **በብሉይ ኪዳን ለጥምቀት ጥላ የነበሩ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረቶች አሉ፡፡**

**1. ኖኅና ቤተሰቡ የዳኑበት ውኃ፤** (ዘፍ. 6.)፡-

- 1ጴጥ. 3፡20-21 ‹‹ኖኅና ቤተሰቡ የዳኑበት›› ‹‹ይህም ውኃ ደግሞ ማለት ጥምቀት ምሳሌው ሆኖ አሁን ያድነናል››



# 2. ግዝረት የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ምልክት ነው (ዘፍ.17፡10)፡፡

- ቃል ኪዳኑ  በስምንት ቀን ልጅና በእግዚአብሔር መካከል የሚፈጸም ነው፡፡ ‹‹የስምንት ቀን ልጅ ይገረዝ›› (ዘፍ.17፡12)፡፡
- ቃል ኪዳኑን ቃል ኪዳን የሚያረገው የህጻኑ የማወቅ ችሎታ ሳይሆን እግዚአብሔር  ራሱ ነው፡፡
- ይህን ቃል ኪዳን የማትጠብቅ ‹‹ያልተገረዘ ቆላፍ ሰው ሁሉ ያቺ ነፍስ ከወገንዋ ተለይታ ትጥፋ ቃል ኪዳኔን አፍርሳለችና›› (ዘፍ.17፡14) እንግዲህ ለዚያ ነፍስ መጥፋት ወላጆችም ከመጠየቅ አይተርፉም፡፡

- ሐዋሪያው ጳውሎስ ‹‹በክርስቶስ መገረዝ በእጅ ባልተደረገ መገረዝ ሆናችሁ ደግሞ የተገረዛችሁ በጥምቀትም ከእርሱ ጋር ተቀበራችሁ›› (ቆላ.2፡11-12)፡፡
- ክርስቲያኖች ሁሉ በዚህ በቁሳዊ እጅ ባልሆነ በመንፈስ ማለትም በጥምቀት ከእግዚአብሔር ጋር ቃል ኪዳን አድርገዋል፡፡
- ግዝረት አንድን ሕጻን የቃል ኪዳን ልጅ እንደሚያደርግ ሁሉ ጥምቀትም እንዲሁ አንድን ሕጻን ይሁን አዋቂ የክርስቶስ አካል ከሆነችው ቤተክርስቲያን ጋር አባል (አንድ) (የእግዚአብሔር ቤተሰብ) ያደርጋል፡፡
- 1ቆሮ. 12፡13 <<አይሁድ ብንሆን የግሪክ ሰዎችም ብንሆን ባሪያዎችም ብንሆን ጨዋዎችም ብንሆን እኛ ሁላችን በአንድ መንፈስ አንድ አካል እንድንሆን ተጠምቀናልና። ሁላችንም አንዱን መንፈስ ጠጥተናል።>>

# 3. ህጻናት የውርስ ኃጢአት አለባቸው፤

- መዝ. 51፡5 <<እነሆ፥ በዓመፃ ተፀነስሁ፥ እናቴም በኃጢአት ወለደችኝ።>>
- **የውርስ ኃጢአት** አንድ ሰው በድርጊት የሚፈጽመው ኃጢአት አይደለም፡፡
- **የግብር ኃጢአት** የሚባለው በኃጢአተኛ ዘር አማካይነት ከአንድ ግለሰብ ልብ ውስጥ የሚወጣ **ክፉ ሐሳብ፣ ክፉ ሥራዎች፣ ክፉ ቃላት** እና የመሳሰሉ ኃጢአቶች ናቸው፡፡
- ህጻን ከእናቱ ማህጸን ጀምሮ ኃጢአተኛ ነው፡፡
- የተጠመቀ ማንኛውም ሰው ግን የኃጢአትን ሥርየት ያገኛል፡፡
- የሐዋ. 22፡16 <<አሁንስ ለምን ትዘገያለህ? ተነሣና ስሙን እየጠራህ ተጠመቅ ከኃጢአትህም ታጠብ።>>
- ስለዚህ ጥምቀት ከውርስ ኃጢአት ያጥባል፡፡

# የሕጻናትን ጥምቀት ተቃዋሚዎች የሚያቀርቡ ነጥቦች፤

- ሕጻናት የውርስ ኃጢአት የለባቸውም ይላሉ፤
  - እንዲህ የምንል ከሆነ ዮሐ. 3፥5 ተሽሮአል ማለት ነው።
- ሕጻናት ማመንና መቀበል አይችሉም ይላሉ፤
  - ለዚህ መልሱ ጥምቀትን ጥምቀት የሚያደርገው እግዚአብሔር ራሱ እንጂ የሰው ዕውቀት አይደለም።
  - በ8ኛ ቀን በሚገረዘው ሕጻንና በእግዚአብሔር መካከል ያለው ቃል ኪዳን የሚጸናው  በሰው እውቀት ሳይሆን በእግዚአብሔር ነው።

# ‹‹ኢየሱስ በ30 ዓመት ዕድሜ ስለተጠመቀ አዋቂዎች እንጂ ሕጻናት መጠመቅ የለባቸውም ይላሉ፡፡

- እኛ የምንጠመቀው ጥምቀትና ኢየሱስ የተጠመቀው ጥምቀት የተለያዩ ናቸው፡፡
  - እኛ የምንጠመቀው ጥምቀት ኢየሱስ ከትንሳኤው በኋላ በማቴ. 28፡19 ላይ ‹‹**ለአህዛብ ሁሉ**›› የታዘዘው ጥምቀት ነው፡፡



- **አንድ ሰው ሳይጠመቅ ገነት ሊገባ ይችላል ይላሉ፤**
  - ሉቃ. 23፡43



# በጥምቀት ምን ጥቅም አለው?

1. የኃጢአት ስርየትን ያስገኛል፤

- የሐዋ. 22፡16 ‹‹አሁንስ ለምን ትዘገያለህ? ተነሣና ስሙን እየጠራህ **ተጠመቅ ከኃጢአትህም ታጠብ**።››
- የሐዋ. 2፡38 ‹‹ጴጥሮስም፡- ንስሐ ግቡ፥ **ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ** እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፤ **የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ**።››

2. ዳግም ልደትን ይሰጣል፤

- ዮሐ. 3፡3 ‹‹ኢየሱስም መልሶ፡- እውነት እውነት እልሃለሁ፥ ሰው **ዳግመኛ ካልተወለደ** በቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም አለው።
- ቲቶ 3፡5 ‹‹እንደምህረቱ መጠን **ለአዲስ ልደት** በሚሆነው መታጠብና (ጥምቀት) በመንፈስ ቅዱስ በመታደስ አዳነን እንጂ እኛ ስላረግነው በጽድቅ ስለነበረው ሥራ አይደለም››

## 3. የእግዚአብሔር መንግሥት ወራሽ ያደርጋል፤

- ዮሐ. 3፥5 እውነት እውነት እልሃለሁ፥ ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር **ወደ እግዚአብሔር መንግሥት** ሊገባ አይችልም።››

## 4. ደህንነትን ይሰጣል፤

- 1ጴጥ. 3፥20-21 ‹‹ጥቂቶች ማለት ስምንት ነፍስ በውኃ የዳኑበት መርከብ ሲዘጋጅ፥ የእግዚአብሔር ትዕግሥት በኖኅ ዘመን በቈየ ጊዜ ቀድሞ አልታዘዙም። ይህም ውኃ ደግሞ ማለት ጥምቀት ምሳሌው ሆኖ **አሁን ያድነናል፥** የሰውነትን እድፍ ማስወገድ አይደለም፥ ለእግዚአብሔር የበጎ ሕሊና ልመና ነው እንጂ፥ ይህም በኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ነው፤››
- ማር. 16፥16 ‹‹ያመነ የተጠመቀም **ይድናል**፥ ያላመነ ግን ይፈረድበታል።››

# 3.2. ቅዱስ የጌታ ራት

- ቅዱስ የጌታ ራት በራሱ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የተመሠረተ በኅብስትና በወይን የተዘጋጀ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛ ሥጋና ደም ነው፡፡



- 1 ቆሮ. 11፡23-25፤ ማቴ. 26፡26-28፤ ማር. 14፡22- 24
- **‹‹ለእናንተ የተሰጠ››፣ ‹‹ለኃጢአት ይቅርታ ለእናንተ የፈሰሰ››**
- ለኃጢአት ይቅርታ፣ ለደህንነት የተሰጠ ቅዱስ ምስጢር ነው፡፡

- የክርስቶስ ሥጋና ደም ከተባረከው ኅብስትና ወይን ጋር **ምስጢራዊ** አንድነት አለው፡፡
- በዚህም ምክንያት ‹‹**ቅዱስ ምስጢራዊ መገኘት**›› ተብሎ ይታወቃል፡፡ ይህም እውነተኛ መገኘት ነው፤ ነገር ግን በህብስቱና በወይኑ በቋሚነት የሚገኝ አይደለም፡፡
- 1ቆሮ. 10፡16 ‹‹የምንባርከው የበረከት ጽዋ **ከክርስቶስ ደም ጋር ኅብረት ያለው** አይደለምን? የምንቆርሰውስ እንጀራ **ከክርስቶስ ሥጋ ጋር ኅብረት ያለው** አይደለምን?››

# የጌታ እራት ለዘላለም ህይወት የተሰጠ እንጀራ ነው።

ዮሐ. 6፡51-58 ‹‹ከሰማይ የወረደ ሕያው እንጀራ እኔ ነኝ፤ ሰው ከዚህ እንጀራ ቢበላ **ለዘላለም ይኖራል**፤ እኔም ስለ ዓለም ሕይወት የምሰጠው እንጀራ ሥጋዬ ነው። እንግዲህ አይሁድ፡- ይህ ሰው ሥጋውን ልንበላ ይሰጠን ዘንድ እንዴት ይቻላል? ብለው እርስ በርሳቸው ተከራከሩ። ስለዚህ ኢየሱስ እንዲህ አላቸው፡- እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ የሰውን ልጅ ሥጋ ካልበላችሁ ደሙንም ካልጠጣችሁ **በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም።** ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ **የዘላለም ሕይወት አለው**፥ እኔም **በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ።** ሥጋዬ እውነተኛ መብል ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነውና። ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ **በእኔ ይኖራል እኔም በእርሱ እኖራለሁ**። ሕያው አብ እንደ ላከኝ እኔም ከአብ የተነሣ ሕያው እንደምሆን፥ እንዲሁ የሚበላኝ ደግሞ ከእኔ የተነሣ **ሕያው ይሆናል**። ከሰማይ የወረደ እንጀራ ይህ ነው፤ አባቶቻችሁ መና በልተው እንደ ሞቱ አይደለም፤ ይህን እንጀራ የሚበላ **ለዘላለም ይኖራል**፡፡››

# ቅዳሴ

# የቅዳሴ ትርጉም

- ቅዳሴ የሚለው ቃል ከግዕዝ የመጣ ሲሆን፤ ምስጋና (ለአምላክነቱ የሚደረግ የምስጋና ሥርዓት)፣ አሠራር፣ አፈጻጸም ማለት ነው።
- በግሪክ /leiturgia/ ‹‹ሌይቱርጊያ›› የሚል ሲሆን በእንግሊዝኛ "Liturgy" ይባላል።
- ቃሉ ከኦርቶዶክስ የተወሰደ ሳይሆን መነሻው ከጥንት ቤተክርስቲያን (ካቶሊክ) ቅዳሴ የተወሰደ ነው።
- በ16ኛው ክፍለ ዘመን በተሐድሶ ጊዜ መጥመቃዊያን አብያተ ክርስቲያናት የጥንት ቤተክርስቲያን ትውፊት ሙሉ በሙሉ ሲያጠፉ ሉተራንና ፕሪስቤትሪያን በቅዳሴ ስርዓት የሚያመልኩ ሆነዋል።
- በ1900 መንቀሳቀስ የጀመሩ ጴንጤቆስጣዊያንም እንደ መጥመቃዊያን ያለ ቅዳሴ ሥነ ሥርዓት ማምለክን መርጠዋል።

- ከጥንት ጀምሮ ምዕመናን በአንድነት ተሰብስበው ያዳናቸውን ጌታ ውለታን እያሰቡ ክብርንና ውዳሴን ለእርሱ የሚያቀርቡበት የሕብረት አምልኮ ‹‹**ቅዳሴ**›› በመባል ይታወቃል፡፡
- የቅዳሴ አገልግሎት የመካነ ኢየሱስን መሠረተ እምነትና ትምህርተ መለኮት የሚገልጽ አገልግሎት ነው፡፡
- ቅዳሴ ሥነ ሥርዓት በቄሶችና ቄስ ባልሆኑ ሰዎችም የሚመራ የአምልኮ ፕሮግራም ቅደም ተከተል ነው፡፡
- ስለዚህ የቅዳሴ አገልግሎት ምዕመናን አዳኝ ለሆነው አምላክ በፍቅር የሚያቀርቡት የምስጋና መስዋዕት ወይም የአምልኮ ሥነ-ሥርዓት ነው፡፡
- ዛሬ ያለን የቅዳሴ መጽሐፍ 40 የሚሆኑ የተለያዩ ሥርዓቶችን አካትቶአል፡፡
- የአዲስ ኪዳን የአምልኮ ሥርዓት-አልባ መሆን የለበትም፡፡ 1.ቆሮ. 14፡26-40

# የእሑድ አምልኮ ሥነ ሥርዓት ክፍሎች

- የእሑድ አምልኮ ሥነ-ሥርዓት በሦስት ክፍሎች ይከፈላል፡፡
- 1. መግቢያ፣ 2. የቃሉ ክፍል እና 3. የጸሎት ክፍል ናቸው፡፡
- 1. መግቢያ፡-
  - መግቢያ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ ስም መጀመርና ሰላምታ ማቅረብ፣ የኃጢአት ኑዛዜ እና የኃጢአት ሥርየት ማስታወቅ፣ ምስጋናና ያካትታል፤ (ቅዳሴ መጽሐፍ ገጽ 29-34፣ ከ1-10)

# የእሑድ አምልኮ ሥነ ሥርዓት ክፍሎች

- **2. የቃሉ ክፍል፡-**

- ይህ አምላክ ካንተ ጋር ይሁን በሚል ሰላምታ ይጀምርና ለቃሉ የሚደረግ ጸሎት፣ ለዕለቱ የተመደቡት ጥቅሶች ንባብ፣ ዝማሬ፣ የወንጌል ክፍል ንባብ፣ የሐይማኖት መግለጫ፣ ለሕጻናት የሚደረግ ጸሎት፣ ስብከት፣ መባ፣ ለመባ የሚደረግ ጸሎት ተደርጎ ያበቃል (የቅዳሴ መጽሐፍ ገጽ 34-38፡ ከ10-20)

- **3. የጸሎት ክፍል፡-**

- ከሰላምታ ይጀምርና የማጠቃለያ ጸሎት፣ የጌታ ጸሎት፣ ተደርጎ በምስጋናና በቡራኬ ስንበት ተደርጎ ይጠናቀቃል (የቅዳሴ መጽሐፍ ገጽ 38-41፣ ከ21-24)

- ከስንብት በኋላ ምዕመናን እየዘመሩ ሲሄዱ አምልኮ የማይቋረጥ መሆኑን ለማሳየት ነው።

# የቤተክርስቲያን ዓመት አቆጣጠር

- የቤተ ክርስቲያን ዓመት በአጠቃላይ በሁለት የሚከፈል ነው።

1. የመጀመሪያው አጋማሽ የበዓላት ዓመት አጋማሽ በመባል ይታወቃል።
   – የበዓላት አመት አጋማሽ ከክርስቶስ ልደት (ከታህሳስ እስከ ሰኔ) ድረስ ያለ ነው።
2. ሁለተኛው አጋማሽ የሥላሴ ዕሑዶችን የሚያከትት የዓመት አጋማሽ ነው።
   – በዓላት የሌሉበት ወቅት ነው። ከሐምሌ እስከ ህዳር ድረስ ያሉት ወቅቶች ናቸው።

# የየእሑዱ ርዕስና ጥቅሶች

- በየወቅቶቹ የሚከናወኑ የእሑድ አምልኮ ሥርዓትና የተመደቡ ጥቅሶች ከቤተክርስቲያን ወቅት ጋር በመያያዝ የተስተካከሉ ናቸው።
- ስለሆነም ታሪካዊ፣ ቲኦሎጂያዊና አስተምህሮአዊ ጠቀሜታቸው በጣም የጎላ ነው።
- ለየእሑዱ የተመደቡ ጥቅሶች ከብሉይ ኪዳን፣ ከአዲስ ኪዳን ከሐዋሪያት መልዕክቶችና (የሐዋ.ሥ) እና ከወንጌል ክፍሎች ነው።

# የጥቅሶች አመዳደብ ያሉት 4 ጥቅሞች

1. በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ማወቅ ከሚገባው የእግዚአብሔር ቃል አብዛኛውን መማር ያስችላል፡፡
2. የቤተክርስቲያኒቱ ምዕመናን የክርስትና ሕይወት አመራር የተቀናጀ እንዲሆን ይረዳል፡፡
3. የቃሉ አገልግሎት ፈር በያዘ እቅድ የሚመራና ምዕመናንን የሚያንጽ ሂደት እንዲከተል… ወዘተ በማድረግ ይጠቅማል፡፡
4. የቃሉ አገልጋዮች ብዙውን ጊዜ በታወቁ ጥቅሶች ላይ ብቻ ከማተኮር ይልቅ የመጽሐፍ ቅዱስ መካከለኛ መልእክት በሆኑ የክርስቶስ ሕይወት፣ ሞት፣ ትንሳኤና እነዚህም ለክርስቲያኑ በሚሰጡት መልእክት ላይ እንዲያተኩሩ ለማድረግ እንደሆነ እንገነዘባለን፡፡

- በዚህ አንፃር ሲታይ የቤተክርስቲያን ዓመትን ተከትሎ የተዘጋጀውን ርዕስና ጥቅሶች በመከተል ማገልገል ቲኦሎጂያዊ መሠረት ይኖረዋል፡፡

# አጀማመር (በሥላሴ ስም)

## የቱ ትክክል ነው?

1. በስመ አብ፣ በስመ ወልድ፣ በስመ መንፈስ ቅዱስ፤ አንድ አምላክ። አሜን።
2. በስመ አብ፣ በወልድ፣ በመንፈስ ቅዱስ ስም፤ አንድ አምላክ ስም። አሜን።
3. በአብ፣ በወልድ፣ በመንፈስ ቅዱስ ስም፤ አንድ አምላክ። አሜን
4. በስመ አብ፣ በስመ ወልድ፣ በስመ መንፈስ ቅዱስ፤ አንድ አምላክ ስም። አሜን።

# ስለ ትክክለኛነቱን ማረጋገጫ መጽሐፍ ቅዱስ ነው፤

- ማቴ. 28:19-20 ‹‹እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።››
- In the name of the Father, and of the Son and of the Holy Spirit. Amen.
- **በአብ፣ በወልድ፣ በመንፈስ ቅዱስ ስም፤ አንድ አምላክ:: አሜን**

# የጠረጴዛው አስፈላጊነትና ትርጉም

- በብሉይ ኪዳን ‹‹መሠዊያ›› በመባል የሚታወቀውን የሚወክል ነው፤ በአዲስ ኪዳን የምስጋና መስዋዕት ብቻ የሚናቀርብበት እንጂ ሌላ የምንሠዋው መስዋዕት የለም። (ዕብ. 10፡12-14)
- በመካነ ኢየሱስ (በሉተራን) በላዩ ላይ የበሩ ሻማዎችና አበባ ያለበት በንጹህ ጨርቅ የተሸፈነ ጠረጴዛ መኖሩ፡-
  1. እግዚአብሔር ታላቅ ንጉሥ ስለሆነ ለንጉሥ አቀባበል የተደረገ ዝግጅትን ያመለክታል፤ (ምድራዊ ንጉሥ የሚገኝበት ጉባኤ እንኳን ያጌጣል)።
  2. የብሉይ ኪዳንን መሠዊያ ያስታውሰናል፤
  3. ትልቅ በዓልና ዝግጅት መኖሩን ያመለክታል፤
  4. የሰውን ልብና መንፈስ ለአምልኮ ያነሳሳል፤
  5. በጸሎት ቤት ውስጥ እንደ ውበት ያገለግላል፤

# የጠረጴዛ፣ የአበባና የሻማና ሌሎች ትርጉሞች በአዲስ ኪዳን



1. **ጠረጴዛው፡-** ጌታ ኢየሱስ የመጨረሻውን እራት ከደቀመዛሙርቱ ጋር የተካፈለበት ጠረጴዛ የሚወክል ሲሆን ትርጉሙ ከጌታና ከእርስ በርሳችን ጋር ያለንን ኅብረት ያመለክታል፡፡
2. **ሻማዎቹ፡-** ብርሃንን ሲያሳዩ ክርስቲያኖች በአምልኮና በምስክርነት የዓለም ብርሃኖች መሆን እንደሚጠበቅባቸው የሚያሳስብ ነው፡፡ ማቴ. 5፡14-15፤
   - 1ኛው ሻማ ኢየሱስን፤ 2ኛው እኛን
3. **አበባው፡-**የፍቅርና የተስፋ ምሳሌ ነው፡፡
4. **በጠረጴዛው ላይ የተቀመጡት መስቀልና መጽሐፍ ቅዱስ፡-** ማንም ሰው ምን እንደሚያምን በቀላሉ እንዲረዳ የሚያደርጉ የተሐድሶ ሥነ መለኮት ማዕከል ናቸው፡፡



5. **ቄሶች የሚለብሱት ነጭ ልብስ፡-** የክርስቶስ አምባሳደርነት ምልክት ሲሆን ምዕመናን ንጹሕ ክርስቶስን መልበሳቸውን የሚያሳስብ ነው፡፡ (2 ቆሮ. 5፡20፤ ገላ. 3፡27)

# ቄስ ማለት ምን ማለት ነው?

- ቃሉ የግዕዝ ቃል ሲሆን በብሉይ ኪዳን (Priest) በአዲስ ኪዳን በግሪክ ኤጵስ ቆጶስ፤ አማርኛ (ጳጳስ/መጋቢ/ እንግሊዝኛ Pastor ማለት ነው፡፡
- ሉተራን Pastor (መጋቢ) የሚለውን ቃል ሲጠቀሙ መካነ ኢየሱስ ቄስ የሚለውን ይጠቀማሉ፡፡ (አገልጋይ ለሚለው የቀረበ ትርጉም አለው፡፡
- ከሽማግሌዎች ጋር ቤተክርስቲያንን በመንፈሳዊ ሕይወት የሚመሩ የቃሉ አስተማሪዎች (መጋቢዎች) ቄሶች ይባላሉ፡፡
  - ‹‹በመልካም የሚያስተዳድሩ ሽማግሌዎች፥ ይልቁንም **በመስበክና በማስተማር** የሚደክሙት፥ እጥፍ ክብር ይገባቸዋል።›› 1 ጢሞ. 5፡17
- ‹‹ቄስ›› ለሚለው ለግዕዝ ቃል በተጨማሪ እንግሊዝኛ Cleric, Chaplain, የሚል ተቀራራቢ ትርጉሞች ያሉት ሲሆን በተለይ (Reverend) የሚለው የተለመደ ሲሆን ቀጥተኛ ትርጉሙ አባ (abba) የሚል ከአክብበሮት ጋር የተያያዘ ነው፡፡

# በቅዳሴ ጊዜ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ትርጉም

- ቄሶች በቅዳሴ ጊዜ ስለሚያደርጉት እንቅስቃሴ ግንዛቤ የሌላቸው ሰዎች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡
- ክርስቲያኖች የአዲስ ኪዳን የመንግስት ካህናት ሆነዋል (1ኛ ጴጥ 2፡9) ፡፡
- የአዲስ ኪዳን ካህናት የሆኑት በኃጢአተኞች እና በእግዚአብሔር መሐል ገብቶ በሞቱ ከአብ ጋር ባስታረቀን በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ወይም በመጠመቅ አዲስ ልደት ያገኙት ናቸው፡፡
- ቄሶች በሚጸልዩበት ጊዜ ወደ ግድግዳ (መሠዊያ/ጠረጴዛ) ይዞራሉ፡፡ ሌላ ጊዜ ደግሞ ፊታቸውን ወደ ምዕመናን ያዞራሉ፤



- ስለዚህ ቄሱና ሕዝቡ በሚጸልዩበት ወይም ኃጢአታቸውን በሚናዘዙበት ጊዜ አብረው ወደ አንድ አቅጣጫ መዞር ያስፈልጋል፡፡
- በጸሎት ጊዜ ከምዕመናን ጋር የእግዚአብሔርን ፊት ይሻሉ፡፡



- ፊታቸውን ወደ ምዕመናን የሚያዞሩት፤ በመዝሙር ጊዜ፣ የኃጢአት ሥርየት ለማሳወቅ፣ በአጠቃላይ ለምዕመናን መልዕክት





# ማማተብ

- ማማተብ በቀኝ እጅ የሚደረግ የመስቀል ምልክት ሲሆን ራስን በሥላሴ ስም መባረክ እንደሆነ ይታመናል፡፡
- ማማተብ ከጥንት ቤ/ክ ዘመን ጀምሮ በክርስቲያኖች ዘንድ የተለመደ ነው፡፡
- የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች በአውራ ጣት በግምባራቸው ብቻ የመስቀል ምልክት እየሠሩ ያማትቡ ነበር፡፡
- በ200 ዓ/ም አከባቢ ከቱኒዚያ ጀምሮ በመለው አፍሪካ የቀኝ እጅ ሙሉ መዳፍን በመጠቀም ከግምባር እስከ ደረት ድረስ በማውረድ ያማትቡ ነበር፡፡
- ተርቱሊያን የተባለው የቤተክርስቲያን አባት ‹‹እኛ ክርስቲያኖች በግምባራችን መስቀል አድርገን እንዞራለን›› ብሎአል፡፡



# ማማተብ

- እየቆየ ሲመጣ ቲኦሎጂካል ትርጉም ተጨምሮበት የመጀመሪያዎቹ **ሦስቱ ጣቶች ሥላሴን** የሚወክል ሆኖ የቀሩት ሁለቱ ጣቶች **የኢየሱስን ሁለት ማንነት** (ፍጹም ሰው ፍጹም አምላክ) አማልካች ሆኖ እስከ ዛሬም ሉተራን ይጠቀሙታል፡፡
- መካነ ኢየሱስ የሉተራንንም እንዲሁም ደግሞ በቀኝ እጅ መዳፍ ያማትባሉ፡፡
- ማማተብ ስለ ክርስቶስ መስቀል የሚያሳስብ እንጂ የተወሰኑ አብያተ ክርስቲያናት ልምምድ አይደለም፡፡
- ማማተብ ክርስቲያኖች ሰማያዊ በረከት ያገኙት በክርስቶስ መስቀል አማካይነት ነው፡፡



# ማማተብ

- በእጅ በሚደረግ የመስቀል ምልክት ስናማትብ የክርስቶስ የማዳኑ ሥራ ተካፋዮች መሆናችንን የምናረጋግጥበት ስለሆነ የመስቀሉን ትርጉም እያሰብን በማስተዋል ማድረግ አለብን፡፡
- ቄሶች በፕሮግራሙ መግቢያና መጨረሻ ላይ የቅድስት ሥላሴን ስም ሲጠሩ የመስቀል ምልክት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡
- ምዕመናንም ጭምር ማድረግ ይችላሉ፡፡ (በሉተራን የተለመደ ነው፡፡)
- ዓላማው የክርስቶስን የመስቀሉ ሥራ ማሳሰብና እና በሥላሴ ስም መጠመቃችንንም ማስታወስ ነው፡፡






1
4
3
2

# እጅ መዘርጋት

- እጅን ዘርግቶ መባረክ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት አለው፡፡

1. አሮን ልጆቼ እስራኤላውያንን እንዲባርኩ እግዚአብሔር የሰጠው ትዕዛዝ ነው፡፡ ዘኁ. 6፡22-25
2. የዘካርያስ ቡራኬ፤ ሉቃ. 1፡68-79
3. ኢየሱስ ደቀመዛሙርቶቹን አጆቹን ዘርግቶ ባረካቸው፡፡ ሉቃ. 24፡50 ‹‹እስከ ቢታንያም አወጣቸው እጆቹንም አንሥቶ ባረካቸው፡፡››

# መልዕክት ክፍሎችንና ወንጌልን ለማንበብ እንዲሁም ለኃይማኖት መግለጫ ለምን እንቆማለን?

- ከብሉይ ኪዳን ዘመን ጀምሮ የእግዚአብሔር ህዝብ ቃሉ ሲነበብ ለመስማትና የኃጢአት ኑዛዜ ለማድረግ ይቆሙ ነበር። ነህ. 8
- መቆም የአክብሮትና የማመስገን ምልክት ነው። ነህ. 8፡5
- በቤተመቅደስ በኋላም በምኩራብ በየሰንበቱ ሰዎች ለአምልኮ ስሰበሰቡ ሕግና ነቢያት በቅደም ተከተል ይነበብ ነበረ። ይህንን እንዲያነቡ አንባቢዎችን የሚመድቡት የምኩራብ አለቆች ነበሩ። ሉቃ. 4፡16፤ የሐዋ. 13፡15፤

- የመልዕክት ክፍል አንባቢዎች ከጉባኤ የሚመደቡ ሲሆን የወንጌል ክፍል ግን ሁል በቅዳሴው መሪ ይነበባል፤
- መልዕክት ክፍል ከተነበበ በኋላ አንባቢዎች ‹‹ይህ የእግዚአብሔር ቃል ነው›› ይላሉ። የወንጌል ክፍል ካነበበ በኋላ ደግሞ አንባቢው ‹‹ይህ የክርስቶስ ኢየሱስ ወንጌል ነው›› ይላል።
- የጥንት ቤ/ክ የሃይማኖት መግለጫዎች የኢ/ወ/ቤ/ክ/መ/ኢ የሃይማኖት መሠረት ስለሆኑ ይህንን ምዕመናን ሁል ጊዜ በቃላቸው በማስታዋል እንዲመሰክሩ ይመከራል።
  - ሮሜ 10፡10 ‹‹ኢየሱስ ጌታ እንደ ሆነ በአፍህ ብትመሰክር እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳስነሣው በልብህ ብታምን ትድናለህና፤ ሰው በልቡ አምኖ ይጸድቃልና በአፉም መስክሮ ይድናልና።››

# ስለ ቀለሞች

- የቄሶች ላንቃ (ስቶላ)፣ የጠረጴዛ (የመሰዊያ) ጨርቅና የፑልፒት ጌጥ ቀለም እንደ ዓመቱ እሁዶች ቀለማት መሠረት መሆን አለበት።
- በሉተራን አብያተ ክርስቲያናት ቀለማት የየራሳቸው ትርጉም አላቸው።
- በሉተራን በጥቅም ላይ ከዋሉ ቀለሞች አምስቱ ብቻ በመካነ ኢየሱስ አገልግሎት ላይ ውለዋል። እነዚህ አምስቱ መሠረታዊ ናቸው ተብለው ይታመናሉ።
- እነዚህም፡- ነጭ፣ ቀይ፣ አረንጓዴ፣ ወይን ጠጅ እና ጥቁር ናቸው። ተጨማሪ ቀለማት ሰማያዊ፣ ደማቅ ቀይ፣ ወርቅማ ናቸው።

# የቀለማት ትርጉምና በጥቅም ላይ የሚውሉ እሁዶች

# ሰማያዊ

- ሰማያዊ ሰማይን ያስታውሰናል፡፡
- ትርጉሙ ከሰማይ የመጣው ኢየሱስ ተመልሶ ወደ ሄደበት ሰማይ ዳግም መጥቶ እንደሚወስደን ያሳስበናል፡፡
- ሰማያዊ ቀለም ተስፋ ያለን መሆናችንን ያመለክታል፡፡
- ሰማያዊ ቀለም መጠቀም የሚገባን ወቅት፡- የቤተክርስቲያን አዲስ ዓመት ማለትም የመምጣቱ 1ኛ እሁድ (ህዳር 30-ታህሳስ 7) ባለው መካከል የሚውል እሁድ፤

# ጥቁር

- የብርሃን እጦትን የሚያመለክት ትርጉም አለው፡፡ (ሐዘን)፤
- የተወሰኑ ጊዜያት ብቻ እንጠቀማለን፡፡
  - ኢየሱስ በተሰቀለ ቀን፤ (Good Friday) ኢየሱስ በተሰቀለ ቀን ጸሐይ ጨልሟልና፤
  - የአመድ ረቡዕ፤ (Ash wedensday)
  - የቀብር ቀን፤
- **Ash wedensday ከዓቢይ ጾም የሚቀድም ረቡዕ ቀን ላይ ይውላል፡፡**
  - ትርጉሙ፡- በሉተራን አብያተ ክርስቲያናት ሰው ኃጢአተኛ መሆኑን፣ ሰው አፈር መሆኑንና ወደ አፈር እንደሚመለስ እንዲያስብ በግምባር ላይ አመድ በመስቀል ምልክት ይደረጋል፡፡

# ወርቅማ

- ወርቅማ ውድነትንና ተፈላጊነትን ያመለክታል፡፡ የክርስቶስ ትንሳኤ ለእኛ እጅግ አስፈላጊና ወሳኝ ውድ ዋጋ የተከፈለበት ጉዳይ እንደሆነ ያመለክታለል፡፡
- ወርቅማ ቀለምን መጠቀም የሚቻለው እንደአማራጭ ለትንሣኤ በዓል እና ለቤተክርስቲያን ዓመት የመጨረሻ እሁድ ነው፡፡

# አረንጓዴ

- አረንጓዴ የእድገትና የልምላሜ ምልክት ነው፡፡ (አረንጓዴ ተክል ሁሉ ይለመልማል ያድጋል)፡፡
- አረንጓዴ የእግዚአብሔር መንግሥት በታላቁ ተልዕኮ እንደሚስፋፋ ያመለክታል፡፡
- አረንጓዴ መንፈሳዊ ብስለትን፣ ደቀመዝሙር ሆኖ ማደግን በጸጋ መለምለምን ያሳያል፡፡



- ክርስቲያን በሕይወት ኖሮ እድገት እያሳየ የሚሄድ መሆኑን ያመለክታል፡፡
- የሚንጠቀማቸው እሁዶች፡- ከጥምቀት በኋላ ያሉ ተከታታይ እሁዶች፣ ከዓቢይ ጾም የሚቀድሙ እሁዶች፣ ከዕርገት በኋላ ያለው እሁድ፣ የቅድስት ሥላሴ እሁድና ከሥላሴ በኋላ ያሉ ተከታታይ እሁዶች፣ ከፍርድ እሁድ የሚቀድም እሁድና የፍርድ እሁድ ናቸው፡፡



# ቀይ

- ቀይ የደም፣ የእሳትና የኃይል ምልክት ነው፡፡
- ክርስቶስ ስለ ሰው ልጅ ኃጢአት ያፈሰሰውን ደም ያመለክታል፡፡
- የኃጢአትን ሥርየትንና ይቅርታን (እርቅን) ያበስራል፡፡
- በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የኢየሱስን ስም ለሌሎች ለማብሰር እንደሚቻል አመልካች ነው፡፡
- ቀይን የምንጠቀመው ለበዓለ ሃምሳ፣ ከበዓለ ሃምሳ በኋላ ያለው 1ኛ እና 2ኛ እሁድ፣ ለሰማዕታት መታሰቢያ በዓል፣ የተሐድሶ ቀን፣ ማቅሰስና ምደባ፣ ለሚስዮን ሥራ መባረክ ቀን ነው





# ሐምራዊ (የወይን ጠጅ)

- በአይሁድ ልማድ ሐምራዊ ቀለም ያላቸው ልብሶች በንጉሳዊያን ቤተሰብ ብቻ የሚለበስ ውድ ልብስ ነበር።
- ስለዚህ ኢየሱስ የአይሁድ ንጉስ መሆኑን ያመለክታል።
- ብርቅና ውድ ሽልማት ሐምራዊ ቀለም ነበር። (ዳን. 6፡7፣16፣29)



- ለአማኞች የሚሰጠው ትርጉም፡- የዘላለም ሕይወት እንድናገኝና ከእርሱ ጋር በአባቱ ዙፋን እንድንነግሥ ውድ ሕይወቱን እንደከፈለ ያመለክታል፡፡
- ለክርስቲያኖች የሚያስተላልፈው መልዕክት፡- አማኝ በዕለት ተዕለት ኑሮው ራሱን ዝቅ አድርጎ በንስሐና በተዋረደ ልብ ልመላለሱ ይገባል የሚል ነው፡፡
- ሐምራዊ (የወይን ጠጅ) ቀለምን የምንጠቀመው፡- የመምጣቱ 2ኛ-4ኛ እሑዶች፣ የዓቢይ ጾም ተከታተታይ እሁዶች፣ የሕማማት ሰሞን ከሰኞ እስከ ረቡዕ እና የዓመቱ መጨረሻ እሁድ ላይ ነው፡፡



# ነጭ

- ነጭ:- የንጽሕና፣ እንከን-አልባ እና የፍጹምነት ምልክት ነው። ‹‹እንደ በረዶ››
- የሚሰጠን ትርጉም:- የኢየሱስ ፍጹምነት የእኛ ሆኖ መቆጠሩን፣ የእርሱ ጽድቅ የእኛ ጽድቅ ሆኖ መቆጠሩን ያመለክታል።



- ነጭን የምንጠቀማቸው ጊዜያት ከሌሎቹ በርከት ያለ ነው።
- የመምጣቱ 1ኛ እሁድ፣ የልደት በዓልና ከልደት በኂላ 1ኛና 2ኛ እሁድ፣ የጥምቀት በዓል፣ ጸሎተ ሐሙስ፣ የትንሣኤ በዓልና ከትንሳኤ በኂላ ተከታታይ እሁዶች፣ የእርገት በዓል፣ የኢየሱስ ወደ ቤተመቅደስ የመግባት በዓል፣ የመስቀል በዓል፣ የጌታ እራትና ጥምቀት፣ የእምነት ማጽኛ ምረቃ፣ መተጫጨትና ጋብቻ።



# ማጠቃለያ፡-

- <u>**መሠረተ እምነታችን (ምን እናምናለን?)**</u>

1. በአብ፣ ወልድ መንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ እናምናለን፤
2. መጽሐፍ ቅዱስ 66ቱ ቅዱሳት መጻሕፍት የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን እናምናለን፤
3. ቅዱሳት ምስጢራት (ቅዱስ ጥምቀትና ቅዱስ የጌታ እራት) የጸጋ መቀበያ መሣሪያዎች መሆናቸውን እናምናለን፤
4. የሃይማኖት መግለጫዎች የእግዚአብሔር ቃል በንጹህ የተብራራባቸው የእምነታችን መሠረት መሆናቸውን እናምናለን፤
5. የቅዳሴ ሥርዓት ለእግዚአብሔር ምስጋና የምናቀርብበትና ጌታ እኛን በቃሉ የሚናገረን በቃሉ የተመሠረተ ሥርዓት መሆኑን እናምናለን፡፡ አሜን!